# <u>የአቶ ዘመን ልብነድንግል አጭር የሕይወት ታሪክ</u>

“በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና፤ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን” (ሮሜ ፲፬፡ ፰)።

አቶ ዘመን ልብነ ድንግል ከአባታቸው ከግራዝማች ልብነ ድንግል ደስታ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ በለጠች ወልደ አረጋይ ጥር 7 ቀን 1944 ዓ.ም. በአድዋ አውራጃ በእንዳ አባ ገሪማ ተወለዱ።

አቶ ዘመን እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አድዋ ንግስተ ሳባ ትምህርት ቤት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ አዲስ አበባ በመሄድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ ብእደ ማርያም ተብሎ ሲጠራ በነበረው የትምህርት ፕሮግራም የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። አቶ ዘመን ባሳዩት የላቀ ውጤት ከአጼ ኃ/ሥላሴ ሽልማት ተቀብለዋል። ከዚህ በተጨማሪ ባገኙት ከፍተኛ የትምህርት ውጤት ወደ ማሳቹሴትስ የቴክኒዮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚያስገባ የፉል ብራይት ስኮላርሺፕ በማግኘት ወደ አሜሪካ በመምጣት የመጀመርያ ድግሪያቸውንና የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል።

አቶ ዘመን ከኤምአይቲ ከተመረቁ በኋላ በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ በመሆን ሰርተዋል። ከዛ በመቀጠል በፎርት ኮሊንስ ኮሎራዶ በሚገኘው የሂውድ ፓካርድ ማእከል ሶፍት ዌር ኢንጂኒየር በመሆን አገልግለዋል። በዚሁ ስራቸውም በኮሎራዶ ለበርካታ ዓመታት የኖሩ ሲሆን የ25 ዓመታት የትዳር አጋራቸውን አግብተዋል።

አቶ ዘመንና ቤተሰባቸው ወደ ሜሪላንድ በመዛወር በሞርጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ የኔትወርክ ኮርሶችን አስተምረዋል። በመቀጠል በዩኒቨርሲቲ ኦቭ ሜሪላንድ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የኢንፎርሜሽን ቴክኒዮሎጂ ማእከል ውስጥ በመቀጠር ጡረታ እስከወጡበት ጊዜ አገልግለዋል።

አቶ ዘመን የትውልድ አገራቸውንና የአገራቸውን ሕዝብ የመርዳት ጠንካራ ፍላጎትና ጉጉት ነበራቸው። የዘውድ አገዛዙንና ከዛ በመቀጠልም ወደ ስልጣን የመጣውን ወታደራዊ መንግስት ለማስወገድ ይደረግ የነበረውን የተማሪዎች እንቅስቃሴ ደጋፊ ነበሩ። ከዚህ በተጨማሪም ከትግራይ ልማት ማሕበር መስራቾች አንዱ በመሆን የሰሩ ሲሆን የተሻለች ኢትዮጵያን ለመመስት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

አቶ ዘመን በፌብሩዋሪ 19 ቀን 2013 በተወለዱ በ61 ዓመታቸው ባደረባቸው ህመም ምክንያት ህክምና ሲከታተሉ ቆይተው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። አቶ ዘመን ከወ/ሮ መብራት ገሠሠ ጋር ትዳር በመመስረት የሦስት ልጆች ማለትም የብዕር፣ የራሔል እና የማርታ አባት ነበሩ።

እግዚአብሔር አምላክ ነፍሳቸውን ያሳርፍልን።